# ዴሞን በዲሞትፌር

የሰው ልጅ በስብዕናው ታሪክ ሰሪነቱንና የታሪክም ወራሽነቱን የተፈጥሮ ባህሪው አድርጎ መኖር ከጀመረ ብዙ ዘመናት አስቆጥሯል። ዘመናቱም እንደየ ዘመናቸው የህብረተሰብ እድገት፦ ዘ-ሬነሳንስ፣ ዘ-ሪፎርሜሽን፣ ዘ-ኢንላይትመንት፣ ዘ-ኢንዳስትሪያል ሪቮሊሲዮን በመባል የየዘመናቸውን ምሁራን ክህሎተ-ጥበብ የታሪክ አሸራቸው አድርገው ሲጓዙ ተስተውሏል። በክህሎተ-ጥበብ መራሂነታቸው ቮልቴርና ጄን ጃኩ ሩሶዎ- የፈረንሳይን፤ ዴቪድ ሁም ጃን ሎክና ዊሊያም ሼክስፒር- የእንግሊዝን፤ ሥፒኖዛ፣ ሄግልና ካርል ማርክስ- የጀርመንን፤ አሌክሳንደር ፑሽኪንና ማክሲም ጎርኪ- የሩሲያን፤ ሊዎናርዶ ዳቬንሲና ሚካኤል አንጀሎም- የጣሊያንን ዝና ዘርተው አልፈዋል።

እናት ኢትዮጵያም እንደ ዘመኗ የህበረተሰብ እድገት በንጉስ ዘራያቆብና በንጉስ ላሊበላ የፍልስፍናና የጥበብ ስልጣኔዋ ግነት የተቀዳጀብት ዘመን ነበር። ጥበብ የእውቀት ብርሃን እንደ መሆኑ ብርሃንም አመለካከትን የሚገራ ሃይል ነውና ዓለማችን ከጭፍን እምነት ወደ አመክኖአዊ አመለካከት የተሸጋገረችው በሊቃነ ጠበብቶቿ ክህሎተ-ጥበብ መሆኑን ዘክረ ታሪክ አስተምሮናል። በዚህ መልክ ለውጥ የምሁራን አሸራነቱን በፈረንሳይ አብዮት፣ በሩሲያ፣ በቬትናም እና በቻይና ህዝባዊ ትግሎች እንዳንጸባረቀው ሁሉ በኢትዮጵያም በደጃዝማች ታከለ ወልደ ሃዋሪያትና በዮፍታሄ ንጉሴ የሪፓብሊክ ጥያቄ የተቀሰቀሰው የለውጥ ነቁጥ በየካቲት ስድሳ ስድስት ተቀጣጥሏል። ድህረ የካቲት "የበረከተ- መርገም" ቅላጼ ፍኖቱ ሲያንጸባርቅ "የዴሞክራሲያና" "የላብ አደር" ጋዜጦችም የለውጥ ነጋሪት ጎስመው በእልፍ አእላፍ ወጣት ምሁርና ገበሬ ተጥለቅልቀው ነበር። የአዲስ ዘመን ጋዜጣም ከጸበሉ ተረጭቶ የስነጽሁፍ ጋን አዘንብሎ "ይጎንጩ አቶ ሃይሌ የገብስ ጥላ ነው ምንም አይሎትም" በማለት የባንዳውን አለቃ በትህትና ያስተናገደበት ወቅት እንደ ነበር ያስታውሷል።

ያ ወቅት የሎሬት ጸጋየ ገብረመድህን ተውኔቶች "ሀ ሁ" በስድስት ወር ሲሉ የጎሕ መጽሄት ቱሉ ፎርሳም የላብ ዋጋውን ከፍ ያደረገበት ዘመን ነበር። በዚያን ወቅት ብዕር ነትቦ አያሌ ቅኔዎች ተዘርፈዋል። ጀግንነት ፍርሃትን አንበርክኮ፣ ብርሃንም ጨለማን ሲገፍ፣ አብሮነትና እኩልነት ሚዛን የደፉበት ዘመን ነበር። የሕዝብና የአገር ፍቅር በዜጎች ልቦና ውስጥ ጠልቀው የተቀበሩበትና፣ ብዕርም ጠመንጃን የማረከበት ዘመን እንደ ነበር የቅርብ ትውስታ ነው። የነ ሎሬት ጸጋየ የብዕር አዝመራ "የእናታለም ጠኑ" አበባው ሲረግፍ በኤሎሄው መስተጋቦ የኢትዮጵያን ህዝብ መስቅ ለመላው ዓለም ይፋ ያደረገበት ዘመን ነበር። ድህረ-የካቲት ጀግናና ቡከን በትግል ሰፌድ ሲበጠሩና ስንዴው ከእንክርዳዱ ሲበራይ የተስተዋለበት ወቅት ነበር።

ሰለስቱ ሃዋሪያት ዮሃንስ ብርሃኔ፣ ተስፋዬ ደበሳይና ጸጋዬ ደብተራው በብዕራቸው ሰርጽ የኢትዮጵያን ወጣት "በዴሞክራሲያ" ጋዜጣ እንደ ፍሬህይዎት - ምርኮኛ ሲያደርጉት ባንዳ ምሁራን ብዕራቸው የዶልዶመ መሆኑን ተገንዝበው "ዴሞን በዴሞትፈር" በማለት ጠመንጃ ወለወሉ። ዓልሙ። ቃታ ሳቡ። በጅምላም ገደሉ። የኢትዮጵያም አየር ገልብጦ ነፈሰና መሬቷን በደም ናጣት። ቀይ ሽብር የወጣት አዝመራውን ገና በአበባው አጨደ። የወላድ ማህጸን ደረቀ። ጎሕ ቀዶ የነበረው ሰማይ ገና ሳይነጋ መልሶ ጨለመ። የህዝብ ትስፋዎች ጠወለጉ። አገሪቱን የምሁር ድርቅ አጠቃትና ኢትዮጵያዊነት ኮስምኖ ሲገኝ ወርሃ - ግንቦት ዘረኝነትን አበለገ። ይህን የቁልቁለት ጉዞ ህዝብ በሃዘን ሲሸኝ -

ገዳዩን ላጤነው አርቆ ሰው ለሚያይ
ባንድ ጊዜ ብዙ ሰው በመማረኩ ላይ
ወረቀት እና እርሳስ ሲሆኑ የበላይ
ሀሊና ማራኪ ብዕር ጦር መሆኑ
ወረቀት ከጥይት ሲደፋ ሚዛኑ
አዲስ ታሪክ ሰርተው ህዝብ ባስተማሩ
ጥቃት በገባቸው ለጠላት ባደሩ
በዲሞትፈር ጥይት በግፍ ተመተሩ

በማለት አንጎራጉሮ ነበር። በቀይ ሽብር ደመና በእኩለ ቀን ጨልማ (darkness at noon) የለበሰው ሰማይና በደም የረዘረዘው መሬት ግን መክኖ አልቀረም። የወላድ ማህጸን በድባቡ ይኑርና አዳዲስ ጸጋዬዎች ተፈጥረው ዲሞትፈርን ሌላ ግዳይ ለመንሳት ዛሬም "የዴሞክራሲያ" ጋዜጣቸው ፍኖቱ ሲደመጥ -

የስራዓቱ ውጋት - ፋኖ
የነጻነት ሸማ - ጃኖ
የፍትህ ሚዛን - የዕኩልነት አልኝታ
የቅኔ መምህር - የኔታ
በአገር ፍቅር - ልቡ የደማ
የለውጥ መርሁ - ካስማ
የጨለማው መቅረዝ - ታጋይ
ያ ደብተራ - ኮክብ ሰማይ
ወደ መቃብር ወርዶ - ተከተተ
ብለን አንመን - አበበ እንጂ - መቼ ሞተ?

የሚል ነው መስተጋቦው።

ሚያዚያ2003